# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን*

ቅጽ 46፣ ልዩ እትም (2) መስከረም፣ 2011


## ኢሕአፓ ትናንት የታገለላቸው ጥያቄዎች ዛሬም ምላሽ ይፈልጋሉ

ለዜጎች እኩልነትና ለሀገር አንድነት በመቆም፣ እኩልነትን ከተነፈጉት ጭቁን የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋርም በመወገን፣ አንገብጋቢ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚያዊና የማኅበራዊ ፍትኅ ጥያቄዎችን በማንሳት፣ ኢትዮጵያን ለማሻሻልና ለማሳደግ ነበር ኅብረብሄራዊው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የታገለው። በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ-መንግሥት በ1964 ዓ. ም ተመሥርቶ ለሦስት ዓመታት በህቡዕ እንዲንቀሳቀስ የተገደደው ኢሕአፓ፣ የፓርቲውን ፕሮግራም በተለያዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አዘጋጅቶና በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍለሀገሮችና በውጭ አገርም ጭምር፣ በአንድ ጀምበር ውስጥ በማሠራጨት ህልውናውን ነሃሴ 26 ቀን 1967 ዓ. ም በይፋ አሳወቀ። ኢሕአፓ ከተመሠረተ እነሆ 46፣ እራሱን ይፋ ካደረገ ደግሞ 43 ዓመታት ሆነው።

በነዚህ ከአራት አሥርተ-ዓመታት በላይ ጊዜ ውስጥ፣ ኢሕአፓ መጀመሪያ በዘውዳዊው አገዛዝ፣ ቀጥሎም ለ17 ዓመታት በደርግ፣ ከዚያም ለ27 ዓመታት በህወሓት/ኢህአደግ የደረሰበትን አፈናና እመቃ ተቋቁሞ ታግሏል። በትግሉም በርካታ ዕንቁ አባሎቹንና ደጋፊዎቹን በመስዋእትነት አጥቷል። ኢትዮጵያዊነትን በማለምለም፣ በዜጎቿ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ አንድነቷን በመጠበቅ፣ ሀገራችን በነፃነት ታፍራና ተከብራ የምትኖር፣ ዘመናዊ፣ ባለፀጋና ፍትኅ የሰፈነባት አገር እንድትሆን በተደረገው የሕዝባችን ያልተቋረጠ ትግል ውስጥ ኢሕአፓ አሌ የማይባል ጉልህ አስተዋጽዖ አበርክቷል።

ፓርቲው ከምሥረታው ጀምሮ የታገለው ኢትዮጵያ የፍትኅና የእኩልነት አገር እንድትሆን ነበር። ይሁን እንጂ በድርቅና በሰው-ሠራሽ ችግሮች ምክንያት የሕዝባችን መቸገር፣ መራብ፣ ዕልቂት፣ በገዥዎች የሚፈጸምበት ግፍና በደል፣ የመብት ረገጣና ወከባ እየሆኑ፣ ኩሩው ሕዝባችንና ታሪካዊቷ ሀገራችን የምትታወቅባቸው የውርደት ማቆሚ ሆኑ። ሀገራችን የባዕዳን ተመጽዋች፣ ሕዝባችን የረሀብና ችጋር ሰለባ መሆንና የዕልቂትና የስደት ዘግናኝ ዜና ኢትዮጵያውያንን ሲያሸማቅቀን ኖረ። ገዥዎች ሕዝቡን ከችጋር መታደግ ባለመቻላቸው ለደረሰው እልቂት ሃላፊነት እንዲወስዱና ሁኔታዎቹም እንዲለወጡ መታገል አስፈላጊ ነበር። በእንቅርት ላይ ጆሮደግፍ እንዲሉ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሌሎቹ ችግሮቹ ያነሱት ይመስል፣ በዘረኛነት የሚገዙት ገዥዎች፣ ለረዥም ዘመናት አብረው የኖሩ ወገኖቻችን በቋንቋ ተከፋፍለው እየተቧደኑ እርስበርሳቸው እንዲጋጩ የፖለቲካ መመሪያ

ጫኑበት። እነሆ ዛሬም በቋንቋ ልዩነት በጋመው ምጣድ ላይ ዳር እስከዳር እየታመሰ ይገኛል።

ሀገራችን የሕዝብ መብት ተከብሮ፣ በልማትና በዕድገት ጎዳና ላይ በመጓዝ ያደጉ አገሮች ከደረሱበት ደረጃ ላይ ለማድረስ በማሰብና በማለም ነበር ኢ.ሕአፓ የታገለው። ኢ.ሕአፓን ያጥላሉ መስሏቸው "ለታላቋ ኢትዮጵያ የቆመው ኢ.ሕአፓ" ያሉም ነበሩ። በሀገራችን የተለያዩ መንግሥታት እየተፈራረቁ የለውጡ ጊዜ ተራዝሞ፣ ያኔ የተነሱት ጥያቄዎች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ፣ ቀጣይ ትግል፣ ተጨማሪ መስዋዕትነት እያስከፈሉ፣ እነሆ አሁን የደረስንበት የተስፋና የስጋት ወቅት ላይ ደርሰናል። ኢ.ሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ ከፍተኛ መስዋዕትነት እየከፈለ የታገለላቸው ሕዝባዊ ጥያቄዎች፣ እስከዛሬ ድረስ ገና ሙሉ በሙሉ መልስ አላገኙም። በመሆኑም ትውልድም በትውልድ እየተተካ ትልቅ ራዕይ ይዞ የተፋለመውን ትውልድ ታሪክ በተገቢው መንገድ ማስተላለፍ የታሪክ ግዴታችን ስለሆነና የጥያቄዎቹን አግባብነት ለማሳየት፣ የጠየቁትን መስዋዕትነት ለመዘከርና እንደገናም ተግባራዊ እንዲሆኑ በጋራ ለመታገል፣ አሁን በአገራችን የተፈጠረውን የዴሞክራሲ ጭላንጭል በመጠቀም ለሕዝባችን የታገልነላቸውን ክቡር ዓላማዎች ቀጥለን እንዳስሳቸዋለን።

## መሬት ለአራሹ

የመሬት ላራሹ ጥያቄ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነሳው በ1960ዎቹ አጋማሽ በተማሪዎች እንቅስቃሴ ወቅት ነበር። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የመሬት ስሪት አብዛኞቹን የሀገራችንን አርሶአደሮች ጭሰኞችና ተጠማኞች ያደረገ በመሆኑ፣ አርሶአደሮች በሚያርሱት መሬት ላይ ያመረቱት ምርት ሙሉ በሙሉ ተጠቃሚ አልነበሩም። የመሬት ከበርቴዎችና ባላባቶች አርሶአደሮቹ ከሚያመርቱት ምርት አብዛኛውን የሚወስዱ በመሆናቸው አፈር-ገፊ ገበሬዎች በድህነትና በችግር ነበር የሚኖሩት። በዚያን ወቅት የነበረው የምርት ግንኙነት ከመሬት ጋር ኑሮውን ያቆራኘውን ከሰማኒያ በመቶ (80%) በላይ የሆነውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአስከፊና ጎስቋላ ኑሮ የዳረገ ነበር። የሀገሪቱም የእርሻ ይዞታ ዘመናዊነት ውሱን ስለነበረ የኢንዱስትሪ ምርትን ለማገዝ ብቃቱ ደካማ ሆኖ ቆይቷል። አብዛኛውን አርሶ-በሌ ጭሰኛ ያደረገው የመሬት ስሪት አገሪቱን በድህነት እንድትኖር ካደረጉ ክስተቶች አንዱ ስለነበር ያ ሁኔታ በትግል መለወጥ ነበረበት። ስለዚህም የኢ.ሕአፓ አባላት ከድርጅቱ መመሥረት በፊትም ጀምሮ የተነሱትን ተራማጅ ጥያቄዎች ከሌሎች ታጋይ ኃይሎች ጋር በማበር "መሬት ለአራሹ" እንዲሆን፣ አስፈላጊው ፖሊሲ እንዲወጣ፣ ዓዋጁ እንዲታወጅና ተፈጻሚ እንዲሆን መራራ ትግል አድርገዋል። ምንም እንኳን በደርግ አምባገነናዊ ሥርዓት ወቅት ሥር-ነቀል የመሬት አዋጅ ቢታወጅም አምራቹን ገበሬ በሚያርሰው መሬት ላይ የባለቤትነት መብት አልሰጠውም። በተጨማሪም አርሶአደሩ የሚያመርተው ምርት በመንግሥት የዋጋ ተመን እንዲሸጥ በመገደዱ ተጠቃሚነቱን በጣም ቀንሶበታል። ከዚህም በተጨማሪ አርሶ አደሩ በበቂ ለማምረትና ቤተሰቡን ለመመገብ እንዲያስችለው በቂ ግብዓት ሊያገኝ አልቻለም ነበር። "ጽድቁ ቀርቶ በወጉ በኮነነኝ" እንዲሉ አዋጁ ከታወጀ ከሁለት ዓመት በኋላ በ1977 ዓ. ም እጅግ ብዙ ወገኖቻችን በረሃብ አልቀዋል። የመሬት ዓዋጁ ብቻውን የአርሶአደሮቹን ሕይወት አላዳነም።

ደርግን የተካው ህወሓት/ኢህአዴግም መሬት የመንግሥት ንብረትነቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል በማድረጉ አሁንም የአርሶአደሩን የመሬት ባለቤትነት መብት አላከበረም። በተጨማሪም የህወሓትና ሌሎች ከመንግሥት ጋር የተወዳጁ ሹሞችና ባለሀብቶች አርሶ አደሩን ከመሬቱ እየገፉ በስርቆትና በዝርፊያ ለውጭና ለአገር ውስጥ ባለሃብቶች በመቸርቸራቸው "የመሬት ቅርምት" የሚባል አዲስ በሙስና የተዘፈቀ ሥርዓት ሊፈጠር ችሏል።

ስለዚህ ዛሬም እንደ ትላንቱ "መሬት ለአራሹ ከሙሉ መብቱ ጋር" እንላለን። አርሶአደሩ የመሬቱ ባለቤት እንዲሆን፣ ከብት አርቢው በህግ የተወሰነ የግጦሽ መሬትና ውሃ እንዲያገኝ፣ ዘመናዊና ሰፊ እርሻዎች በፌደራል መንግሥቱና የፌዴሬሽኑ አባላት በሆኑት አሃዶች ስምምነት ለኅብረተሰቡ ልማት በሚያመች መልኩ እንዲስፋፉና በህገ-ወጥ መንገድ በሥልጣን የተመኩ ዘራፊዎች የተቀራመቱት መሬት ለባለቤቱ እንዲመለስ እንታገላለን።

## ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ያለገደብ

ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች ያለገደብ የሚለው የትግል መፈክር፣ የመንግሥት ሥልጣን ገደብ በማይታወቅበት አገር፣ መንግሥት ተፎካካሪ ፓርቲዎችንና በራሳቸው ነፃ መንገድ የተደራጁ የብዙሃንና የሲቪክ ማኅበሮችን በጠላትነት ፈርጆ በሚያሳድድበት አገር፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱን መንግሥት ሊመርጥና ሲያሻው ደግሞ ሊያወርድ በማይችልበት አገር፣ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ህጋዊና ህገ-መንግሥታዊ እውቅና እንዲኖራቸው ለማድረግ ያታገለ መፈክር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ በነፃ መሰብሰብ አይችልም ነበር። በነፃ ተደራጅቶ የመረጠው የፖለቲካ ይሁን የብዙሃን ድርጅት አባልና አመራር የሚሆንበት ዕድል አልነበረም። ቅሬታውን ወይም ድጋፉን በሰላማዊ ሰልፍ የሚገልፅበት ዕድልም አልነበረም። መብት ነበረ ከተባለም፣ መንግሥት እንዳሻው ትንሽ እዚህ፣ ትንሽ እዚያ የሚሰጥበትና ራሱ ግን ተጠያቂ ያልሆነበት ሥርዓት ነበር የነበረው።

ስለዚህ ዛሬም እነዚህ መብቶች ያለምንም መሸራረፍ የዜጎች መብቶች መሆናቸው መታወቅና መከበር አለባቸው ይላል ኢሕአፓ። የፌደራል መንግሥትና ሌሎችም መንግሥታዊ አካላት የሀገራችን ዜጎች ባሻቸው የሀገሪቱ ክፍሎች የመኖርና ሃብት የማፍራት መብታቸው መሆኑን መገንዘብ፣ ማክበርና ማስከበር አለባቸው። ዜጎች እንደ ሁለተኛ ደረጃ ዜጋ የሚታዩበት፣ በስጋትና በመፈናቀል የሚሰቃዩባት ኢትዮጵያ፣ ለዜጎቿ ሙሉ ዴሞክራሲያዊ መብት አጎናጽፋለች ለማለት ስለማይቻልና እነዚህ ችግሮች አሁንም አፍጥጠው ስለሚታዩ እነሱን ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ ትግሉ ያለማሰለስ መቀጠል አለበት።

## የብሄረሰቦች የእኩልነት መብት መታወቅ

ኢሕአፓ ከመመሥረቱና በይፋ ከመታወቁ በፊት ጀምሮ በኢትዮጵያ "ፍትህ አላገኘንም" ብለው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚታገሉ ወገኖች ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ በኤርትራ፣ በጎጃም፣ በባሌና በኦጋዴን የተደረጉ ትግሎች ይጠቀሳሉ። በትግራይ ውስጥም የመጀመሪያው “ወያኔ” በሚል መጠሪያ የሚታወቅ የአርሶ አደሮች ተቃውሞ ነበር።

ማንኛውም በሀገራችን ውስጥ የሚገኝ የኅብረተሰብ ክፍል፣ ጭቆና አለብኝ፣ መብቴ አልተከበረም ብሎ የሚሰማውን ጭቆና ሲቃወም፣ የተነሳውን ጥያቄ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ ገጽታዎች መመርመርና መገንዘብ፣ የሀገርና የሕዝብን አንድነትን አስጠብቆ ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ መደገፍ ተገቢ ነው ብሎ ኢሕአፓ ያምናል። ኢሕአፓ፣ ኢትዮጵያ ሀገራዊ አንድነቷ የተከበረ ዴሞክራሲያዊት አገር እንድትሆን እያስተማረ፣ በተያያዥ ደግሞ የብሄረሰቦች ቋንቋና ባህል እንዲከበር አስተምሯል። በመሆኑም የጠንካራ ኢትዮጵያዊነት አመለካከቱና ራዕዩ ካላስደሰታቸው ጠባብ ብሄርተኞች በኩል ኢሕአፓ ከፍተኛና ተከታታይ ጥቃት ደርሶበት ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል።

በሕዝባችን ላይ እንደዛሬው ከቀየው መፈናቀል ሳይስፋፋ "ኢሕአፓ ከትግራይውጣ" በሚል የጠባብ ብሄርተኝነት አመለካከትና እብሪት በህወሓት ጥቃት ደርሶበት፣ ኢሕአፓ ትግራይን በጦርነት ለቅቆ እንዲወጣ የተገደደ የመጀመሪያው በሀገሩ ውስጥ ተሰዳጅ የተደረገ ድርጅት ነበር። ኢትዮጵያችን የሁሉም ዜጎቿ የጋራ ሀገር መሆኗን ስለሚያምን፣ ህወሓት/ኢህአዴግ በፈጠረው ሥርዓት ምክንያት በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ፣ በኦሮሞዎች፣ በወላይታዎች፣ በጉራጌዎች፣ በአኙዋኮች፣ በተለይም ደግሞ በልዩ ትኩረት በአማራው ማኅበረሰብ ላይ ያነጣጠረ ጥቃት ሲያደርስ ኢሕአፓ ጥቃቶቹን ተቃውሟል። በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ውስጥ በሚኖሩ ትግርኛ ተናጋሪዎች ላይ የሚደርስ ማንኛውንም ጥቃት ይቃወማል።

ጠባብ ብሄረተኛነትና ይፋ የሆነ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ የሀገር መመሪያ ሲሆን፣ በተለያዩ ስሞች ተሞካሽቶ፣ በጭምብሎቹም ተጀቡኖ፣ ትልቁን ኢትዮጵያዊነት ሲበክልና ሲመርዝ፣ የመገንጠል አንቀጽ በህገ-መንግሥት ውስጥ ሲካተት፣ ሀገራችንን በማይታበል ደረጃ የከባድ ችግር ሰለባ አድርጓት ቆይቷል። በቅርቡ፣ በጉራፈርዳ፣ በቤነሻንጉልና ሌሎችም አካባቢዎች የታየውን የአማራውን ማኅበረሰብ ተወላጆች የማፈናቀል ተግባር፣ የኦሮሞ ማኅበረሰብ ተወላጅ ኢትዮጵውያን ከኢትዮጵያ ሶማሌ "ክልል" መፈናቀል፣ እንዲሁም በሁለቱም "ክልሎች" ድንበር አካባቢ በተከታታይ የተፈጸሙት ደም አፋሳሽ ግጭቶች እጅግ አሳዛኝ ድርጊቶች ናቸው።

በደቡብ በሲዳማና ወላይታ እንዲሁም በጌዲኦና ጉጂ...ወዘተ መካከል በቅርቡም በጥፋት ኃይሎች አቀነባባሪነት በጂጂጋ በክርስቲያኖችና ኢትዮጵያዊ ሶማሌ ባልሆኑ "ሌሎች" በሚባሉት ዜጎች ላይ የደረሰው አሳዛኝ ግድያና የንብረት መውደም፣ በወልቂጤም የርስበርስ ግጭቶችና ተመሳሳይ ተግባሮች መፈጸማቸውም ቀጠለ። የተፈጸሙትን ጥቃቶች ሁሉ አውግዘናል። ውግዘት ብቻ ግን አይበቃም። እንደዚህ ዓይነቶቹ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች በማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ት ዜጋ ላይ እንዳይፈጸሙ በጋራ ታግሎ ማስቆም ያስፈልጋል። በኢትዮጵያ ሀገራዊ ድንበሮች ውስጥ በማንኛውም አካባቢ የሚኖር ዜጋ ባለ ሙሉ መብት ኢትዮጵያዊ/ት እንዲሆን/እንድትሆን ሁላችንም ጥብቅና ልንቆም ይገባናል ይላል ኢሕአፓ!

በኢትዮጵያችን ውስጥ ላለፉት 27 ዓመታት ለታዩትና ዛሬም ላላባሩት የእርሰ በርስ ፍጅቶች፣ በእኛ ዕምነት መሠረታዊ መነሾው የጎሳና የቋንቋ ፌደራሊዝሙ ነው። ዕውን እኛ ኢትዮጵያውያን በቋንቋዎች ብቻ የምንገለጥና በነሱም የተካለልን ነን? ይህ በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ከፋፋይ ፌደራሊዝም እጅጉን ጎጂ ስለሆነ ክፍለሀገርን መሠረት ባደረገ፣

በተማረ የሰው ኃይል ብዛት ኋላ የቀሩ የሀገሪቱ ክፍሎችን ዕድል በሚሰጥ መንገድ የተዋቀረና የሕዝቦችን ታሪካዊ ትስስር እሳቤ ውስጥ ያስገባ ፌደራላዊ አወቃቀር ያስፈልጋል። ስለሆነም አሁን አገሪቱ በቋንቋ የተከፋፈለችበት የጎሣ ክልል ፈርሶ በጥናት በተደገፈ የክፍለሀገሮች (የአስተዳደር ክፍሎች) መዋቀር አለባት ብሎ ኢ.ሕአፓ ያምናል። በዚህ ዙሪያ ያለውን ራዕይ ከባለድርሻዎች ጋር ለመወያየት ዝግጁ ነው።

## ፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር

አገራችን ኢትዮጵያ ከደሃ አገሮች ተርታ ከተመደበች ምዕተ-ዓመታት አልፈዋል። የሀገሪቱ እድገት በድርብ አሃዝ እየጨመረ ነው ቢባልም፣ ይህ ትርክት ከእውነት ጋር በማይተዋወቅ መንግሥት እየተደረተ የሚቀርብ ስለነበር ተዓማኒነት አልነበረውም። መንግሥት የሚለውን እንቀበል ብንል እንኳን ሀገራችን ውስጥ ድህነት እየቀነሰ አይደለም። ድርቅ እየተመላለሰ እያጠቃን ነው። የመሬት ቅርምት በተካሄደባቸው አካባቢዎች፣ መሬታቸው የተነጠቀባቸው አፈር ገፊዎችና ከብት አርቢዎች ወደባሰ ድህነት ውስጥ ገብተዋል። አብዛኛው የሕዝብ ክፍል ወጣቶች ሆነው ሳሉ የወጣት ሥራ-አጥነት ችግር ከመቼውም በላይ አስጨናቂ የማኅበራዊ ጉዳይ ሆኗል። ከዚህ ሌላ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ቀውስ፣ ድርቅንና ጎርፍን እያፈራረቀ ሁኔታዎችን ይበልጥ እንደሚያባብሰው ደግሞ መገመት ይገባል። አርሶአደሩ የገጠሩ ኑሮ ተስፋ አስቀራጭ እየሆነበት ሲሄድ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ከተማ የሚጎርፈው ሕዝብ ከተሞችን ከማጨናነቅ ጋር የከተማ ድህነትን ያስፋፋል።

በሌላ በኩል ደግሞ የሀገሪቱ ሃብት በጥቂቶች እጅ እየተከማቸ ነው። ሙስና በእጅጉ ተስፋፍቷል። በሙስና የተዘረፉ ንብረትና ገንዘብ ተመልሰው ለድሆች ማቋቋሚያና ለሥራ-አጦች ሥራ መክፈቻ እቅዶች እንዲውሉ መታገል ይገባል። በሃብታሞችና በድሆች መካከል ያለው የሃብት ልዩነት እየሰፋ ነው። የከተማ ኗሪ ድሃ ዜጎችን በስመ የከተማ አዲስ ፕላን ቤቶቻቸውን በማፍረስና ሃብታሞች የሚኖሩባቸውና የሚዘርፉባቸው ህንፃዎች በምትካቸው በመሥራት ብዙ ድሆች የጎዳና ተዳዳሪዎች ሆነዋል። የየራሳቸው ትንንሽ ጎጆዎች የነበሯቸውን ወገኖቻችንን መሬታቸውን በመንጠቅ ጎዳና ተዳዳሪዎች ያደረጉት በጨካኝና ዘራፊ ገዥዎች መዳፍ ሥር ተበዳዩ ዜጋ የሚዳሸቅባት፣ በልማታዊ መንግሥቷ ሥር በርካታ ቆሼዎችን እየፈጠረች ያለች ሀገር ሆናለች ሀገራችን።

ኢ.ሕአፓ ዛሬም መንግሥት በግብር ፖሊሲ፣ በማኅበራዊ-መረብ ፖሊሲና በመሳሰሉት ድህና የተጎሳቆሉ ዜጎችን ሰብዓዊ ክብራቸውን እንዲመልስላቸው፣ እንዲደጉማቸው አበክሮ ይታገላል።

## ሕዝባዊ መንግሥትን መመሥረት

የየካቲት 1966 ዓ. ም ሕዝባዊ አብዮት ሲፈነዳ፣ ከተነሱት ዋና ዋና ጥያቄዎች አንዱ ኢትዮጵያ ከዘውድ አገዛዝ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክነት አንድትለወጥ የሚጠይቅ ነበር። በመጀመሪያ ለለውጡ አጋዥ የነበረው የዝቅተኛ ወታደሮች ክፍል፣ የሕዝቡን የለውጥ ጥያቄና የራሱንም ውስጣዊ ችግሮች እያነሳና መልስም እያገኘ ሲሄድ፣ በሚመጥን ደረጃ ሌላ የተደራጀ ኃይል ስላልነበረ፣ ወታደራዊ ጉልበቱን ተጠቅሞ መስከረም 1967 ዓ. ም የወታደራዊ መንግሥት ተመሠረተ። እስኪዚያን ጊዜ ድረስ በነበሩት ሰባት ወራት ውስጥ

ሕዝቡ በትግሉ የተጎናፀፋቸውን ድሎች በአንድ ምሽት በወታደሮች ተነጠቀ። ሰላማዊ ሰልፎች ታገዱ፣ የመፃፍና የመሰብሰብ መብቶች በወንጀልነት ተፈርጀው የሚያስቀጡና የሚያስገድሉ ሆኑ፣ ሌላው ቀርቶ የጻፈ ብቻ አይደለም “ያሰበንም” ወንጀለኛ የማድረግና በሞት የሚቀጣ፣ ጥፋተኛ የሚያደርግ አዋጅ ወጣ።

ኢሕአፓ ከምልዓተ-ሕዝቡ ጋር በመሆን የወታደራዊ መንግሥትን እብሪት መቃወም ጀመረ። በወታደራዊ መንግሥት ምትክ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት እንዲቋቋም ጠየቀ። ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥቱም የሽግግር መንግሥት ሆኖ በሕዝባዊ ምርጫ ቋሚ መንግሥት እስኪመሠረት ድረስ አገሪቱን እንዲያስተዳድር አሳሰበ። የጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥቱን የሚመሠረቱትን ክፍሎችን አመላከተ። በወቅቱ ማኅበሮች ከነበራቸው ከመምህራን፣ ከሠራተኞች፣ ከተማሪዎች፣ ከወታደሮች፣ ከነጋዴዎች፣ ከብሄረሰብ እንቅስቃሴዎችና ከአገር አቀፍ የፖለቲካ ድርጅቶች…ወዘተ ተውጣጥቶ እንዲመሠረት ጥሪ አቀረበ።

ኢሕአፓ፣ በወቅቱ ዝነኛና በስፋት ተነባቢ በነበረው የፓርቲ ልሳኑ በዴሞክራሲያ፣ በተደጋጋሚ ይህን የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ አስተጋባ። የወታደራዊው መንግሥት ራሱን ጊዜያዊ ብሎ ሕዝብን ሊሸንግል ሲሞክርም ኢሕአፓ ስለጊዜያዊነቱ የሚናገረው እውነት እንዳልሆነና ቋሚ እንደሚሆንም ይናገር ነበር። እንደተባለውም በሕዝብ ትግል ከ17 የግፍ ዓመታት በኋላ እስኪፈራርስ ድረስ፣ ወታደራዊ መንግሥቱ ከጊዜያዊነት ወደ ቋሚነት፣ በኢሠፓአኮና በኢሠፓ አማካይነት ሕዝቡን እያዳሸቀ ቆይቶ ነበር። የተለያዩ የኅብረተሰቡ ክፍሎና ኢሕአፓ ላቀረቡት የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄና ሥልጣን የሕዝብና ከሕዝብ የሚገኝ መሆኑን ሳይቀበል እምቢኝ እንዳለ ሕዝብን ሲያሰቃይ ቆይቶ ቀድመውት እንዳለፉት አስተዳደሮች ሁሉ ደርግም አለፈ። አምባገነናዊው ደርግ የዚያን ትውልድ የነቃውን ክፍል ፍጅቷል። ይሁን እንጂ ኢሕአፓ በቀልን የማይሻ በመሆኑ፣ በተለይም ዛሬ ኢትዮጵያችንን ማዳን ባለብን ወቅት በይቅርታ መንፈስ ተባብሮ መታገል ስለሚገባ፣ ኢሕአፓ ሁሉንም ይቅር ይላል፣ የኢሕአፓ አባላት ልብ ሠፊም ይቅር ባይም ነውና።

በሌላ በኩል ደግሞ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ ከመውጣቱ በፊትና ሥልጣን ከያዘም በኋላ፣ የደርግን ኃጢያት ነጋ ጠባ እያነበነበ ከወታደራዊ መንግሥት በማይተናነስ መልክ በሥልጣን ለመቆየት ሲል ሕዝቡን በዘር እየከፋፈለ፣ ለይስሙላ በህገ-መንግሥቱ ባሰፈራቸው መብቶች ጭምብል ለ27 ዓመታት የሀገር ሃብት ሲመዘብርና ሕዝባችንን ለሰቆቃ ሲዳርግ የከረመ ሥርዓት መሥርቶ እንደነበር ፀሐይ የሞቀው እውነታ ነው።

ባጥቂት ዓመታት ጭቆና በቃኝ ብሎ በአገሪቱ ውስጥ የተነሳው የለውጥ ማዕበል ኢህአዴግን በኃይል በሚያናውጥበት ወቅት፣ አሁን ወደ ሥልጣን የመጡትን ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር አብይ አህመድን ጨምሮ የ”ለማ ቡድን” በመባል የሚታወቀው፣ እነ አቶ ገዱንም ያካተተ ኃይል፣ በኢሕአዴግ ውስጥ ብቅ ማለቱን ተከትሎ አገራችንን ተስፋ የሚሰጧት፣ የበጎ ለውጦች ጭላንጭል እያየች ነው። እነዚህ የለውጥ ኃይሎች የሚናገሯቸው ቃላትና እየወሰዷቸው ያሉት እርምጃዎች ተስፋ ሰጭዎች ናቸው። ሆኖም ለውጦችን በማይናወጥ መሠረት ላይ ለማቆምና አሁንም እየታዩ ያሉትን የዜጎች መብት ጥሰቶች ለማስቆም፣ የሕዝባዊ መንግሥት መመሥረትና የዴሞክራሲ ዋልታ የሆኑ ተቋሞችን በጽኑ መሠረት ላይ መትከል ምትክ የሌላቸውና ለነገ የማይባሉ ሥራዎች ናቸው። ይህን ውስብስብ ችግር

ቀርፎ የሚታሰበውን ለውጥ ኢህአዴግ ብቻውን ዕውን ሊያደርገው አይችልም ብልን እናምናለን። ስለዚህ ኢሕአፓ ከጠቅላይ ሚንስትሩ፣ ከ"ቡድን ለማ"ና ከሌሎችም የለውጥ ኃይሎች ጋር በመሆን ይህ የለውጥ ሂደት ጽኑ መሠረት ላይ እንዲቆም ይታገላል።

ኢሕአፓ ከምሥረታው ጀምሮ ለ46 ዓመታት የታገለላቸው ጥያቄዎች ዛሬም ህያውና መልስ ፈላጊ ናቸው። ኢሕአፓን ከሌሎች ተፎካካሪ ፓርቲዎች ልዩ የሚያደርጉትን በታሪኩ የታገለላቸውን የማኅበራዊ ፍትኅ ጉልህ ጥያቄዎችና ለዴሞክራሲያዊ መብቶች በሙሉ መከበር ከሕዝባችን ጎን ቆሞ ያለማቋረጥ መታገሉ ነው። ኢሕአፓ ባነሳቸው ጥያቄዎች ዙሪያ ከሕዝብ ጎን ተሰልፎ፣ ለመታገልና ተግባራዊ ለማድረግ ዛሬም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቁርጠኝነቱን ያረጋግጣል። ዓላማዎቹ ዛሬም የማይናወጡ ናቸውና በአዲስ ተረካቢ ኃይሎች አራማጅነት ጎልው ሆነው ወደፊትም ለምልመው እንደሚቀጥሉም ያምናል። ተረካቢ የሚሆኑት የወጣቱ ትውልድ አባላት ጥያቄዎች አስፈላጊም፣ ጠቃሚም፣ የማይታለፉም፣ የእኛም ጥያቄዎች ናቸው ብለው እንዲያራምዷቸው አበክረን እንጥራለን።

የኢሕአፓ ራዕይ ዛሬ ማኅበራዊ ፍትኅን መሠረት ያደረገ የሶሺያል ዴሞክራሲ አማራጭ ነው። ይህ አማራጭ እንደ ፖለቲካ ፍልስፍና በሰፊ ዴሞክራሲ፣ ሕዝቡን መብት በሚያቀዳጅ መልኩ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ ሰልፍ የማድረግ...ወዘተ መብቶችን ያቀፈና ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆኑም የሚያታግል ነው። ኢሕአፓ የጠባብ ቡድን አምባገነንነትን በእጅጉ ይጠላል። በ1976 ዓ. ም ቋራ ላይ ካደረገው ከሁለተኛ ጉባዔው ጀምሮ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሥርዓት፣ ከአንድ "እኔ ብቻ አውቅልሃለሁ" ከሚል አውራ ወይም "ግንባር ቀደም" አምባገነናዊ ፓርቲ ወደ መድብለ-ፓርቲ እንዲሸጋገር ቀደም ብለው አቋም ከያዙትና ከታገሉት ድርጅቶች በቀዳሚነት የሚጠቀስ ነው።

በኤኮኖሚና ማኅበራዊ ገጹ ደግሞ የሶሻል ዴሞክራሲ እምነት በበዝባዥ ገዥዎች፣ በኅሊናቢስና ስግብግብ ዘራፊዎች፣ ተመዝብረው ድሆች የተደረጉት ዜጎቻችን፣ ሙሉ በሙሉ የዜግነት መብታቸው እንዲታወቅና እንዲከበሩም፣ የጉልበታቸው ዋጋም ባለቤቶች እንዲሆኑ የሚጥርና የሚተጋ አማራጭ ነው። ኢትዮጵያዊ ቤተሰብ ጠግቦ በልቶ ካላደረ፣ ንጹህ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የኤሌክትሪክ መብራት፣ ህክምናና የትምህርት ዕድሎች ካላገኘ፣ የዜግነት ትርጉሙ ምኑ ላይ ነው? ብለን እንጠይቃለን። የበይ ተመልካችና ተመፅዋች መሆን ከቶ እንደ ዜጋ ሊያስቀጥር ይችላልን? በእኛ እምነት በሀገራችን ፍትኃዊ የሃብት ክፍፍል እንዲኖር፣ መንግሥት ለሥራ-አጦች ሥራ እንዲፈጥር፣ ሥራ ሲያጡም ለመኖር እንዲችሉ በቂ ማኅበራዊ ዋስትና ለመስጠት እንዲችል፣ ድህነትን ለማጥፋት ያላሰለሰ ትግል እንዲያደርግ፣ በሃብታምና በድኃ መካከል ያለውን ልዩነት ለማጥበብ ሁሌም ያላሰለሰ ጥረት እንዲደረግ አጥብቀን እንታገላለን። ኢትዮጵያ ሀገራችን ሁሉም ዜጎችዋ ማኅበራዊ ፍትኅ አግኝተው በእኩልነትና በሠላም እንዲኖሩ ማድረግ እንፈልጋለን። ሀገራችን ኢትዮጵያ አድጋና በልጽጋ እንደ ቀድሞ ገናናነቷንና ዝናዋን አድሳ፣ አንድነቷን ጠብቃ ዜጎቿ ታፍረውና ተከብረው ከሚኖሩባት የዓለም አገሮች ተርታ ትገባለች ብለን በጽኑ እናምናለን። ለዚህም ያለማሰለስ በርትተን ለመታገል ለምንወደውና ለምናከብረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዛሬም የማይታበል ቃል እንገባለን።

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እናቸንፋለን!